## ማሻሻያ

አንቀጽ 5-ሀ-3

3.1 እድርተኛው ወይም እድርተኛዋ ከአሜሪካን ውጪ ሄደው የሞት አደጋ ቢያጋጥማቸው በዚህ ደንብ አንቀጽ 5-ለ-1 መሠረት ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

3.2 የእድርተኞቹ ልጆች ስማቸው በአባልነት ፎርም ላይ የተመዘገቡ፣ እድሜያቸው ከ26 ዓመት ያልበለጠ፣ ትዳር ያልያዙና ለኮሌጅ ትምህርት የሚሄድ፣ ከአሜሪካ ውጪ ሄደው የሞት አደጋ ከደረሰባቸው ፣ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5-ለ-2 መሠረት ተገቢው እርዳታ ይደረግላቸዋል።

3.3 በእድሜም ሆነ በአካል ጉዳት(disability) ሥራ መሥራት የማይችል ፣ ከዕድርተኛው ጋር የሚኖር ፣በአባልነት ፎርም ላይ የተመዘገበና በታክስ ክሌም (Tax Claim) የተደረገ የቤተሰብ አባል የሞት አደጋ ቢደርስበት ፣ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5- ሀ- 1 መሠረት ተገቢው እርዳታ ይደረግለታል።

3.4 ማንኛውም በእድርተኛው ቤተሰብ ፣በጥገኝነት የተመዘገበ(ች) የቤተሰብ አባል ከአሜሪካን ውጪ ሄደው የሞት አደጋ ቢያጋጥማቸው በዚሁ ደንብ አንቀጽ 5-ለ-2 መሠረት ተገቢው እርዳታ ይደረግለታል።

4.1 በዚህ ደንብ አንቀጽ 5-ሀ ተራ ቁጥር 4 የተጠቀሰው በአንቀጽ 5-ሀ-1 መሠረት የሚሰጠው ድጋፍ እንደተጠበቀ ሆኖ የዕድርተኞቹ እናት ወይንም አባት ከአሜሪካን ውጪ ሄደው የሞት አደጋ ቢያጋጥማቸው በዚህ ደንብ አንቀጽ 5ለ2 መሠረት ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

## አንቀጽ 1

4 የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ በተመለከተ ፣ የስብሰባው ጥሪ የሚደረገው ስብሰባው ከመደረጉ 15 ቀናት በፊት ፣ በቤተክርስቲያናችን አውደምህረት ላይ ይሆናል።

5 በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ የጠቅላላው ጉባኤ ስብሰባ ጥሪ ለሁለተኛ ጊዜ በተከታታይ ተጠርቶ ምላተ ጉባኤው ካልተሟላ ፣ ለሶስተኛ ጊዜ ጥሪ ተደርጎ በተገኘው አባላት ስብሰባው ይካሄዳል ፤ የሚወሰነውም ውሳኔ ጠቅላላው ጉባኤ እንደወሰነው ተቆጥሮ ሥራ ላይ ይውላላ።